④ The masthead

# ርእሰ አንቀጽ



## ወቅቱ የተግባራዊ ትግል ነው!

ለገዛ ራሱ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እና ለኢትዮጵያ ቅን የሚመኝ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ህወሓትን ለማስወገድ ተግባራዊ ትግል ውስጥ መሳተፍ የሚኖርበት ወቅት ላይ እንገኛለን። በዚህ ወሳኝ ወቅት ከዳር ሆኖ መታዘብ ዘረኛውን፣ አምባገነኑን፣ ፋሽስቱን ህወሓት እንደመደገፍ ይቆጠራል።

ዛሬ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ህሊናውና አቅሙ በሚፈቅድለት የትግል ዘርፍ የመሰማራት ሰፊ እድል ተፈጥሮለታል። በዚህም መሠረት የህወሓትን አፈና በጠነከረ ክንድ ለመመከት የቆረጡ ኢትዮጵያዊያን ወደ በረሃዎችና ተራራዎች አቅንተዋል። ብዙዎች በመንገዱ ላይ ያሉ ጋሬጣዎችን ተቋቁመው እየተቀላቀሏቸው ነው። በደል የመረራቸው ሌሎች በርካታ ኢትዮጵያዊያን በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በቡድን ለነፃነታቸው ዘብ ቆመው በህወሓትና አገልጋዮቹ ላይ እርምጃ መውሰድ ጀምረዋል። ይህ የሚበረታታ እና ተቀናጅቶ ሊጠናከር የሚገባው ጉዳይ ነው።

አሁን ያለንበት ጊዜ ልዩ የትግል ወቅት ነው። ትናንት በከተሞች ይካሄድ የነበረው ፀረ ወያኔ ትግል ዓይነተኛ መታወቂያው ሕዝባዊ ተቃውሞ ነበር። ዛሬ ግን ይህ ሁኔታ ተቀይሯል። በተለይ በአገዛዙ ፈቃድ የሚደረጉ ተቃውሞዎች ፋይዳ ቢስ ሆነዋል። በአገዛዙ ፈቃድ በሚደረጉ ተቃውሞዎች ለውጥ እንደማይመጣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በማያሻማ ሁኔታ ተረድቷል። ስለሆነም ትግሉ ወደ ሕዝባዊ እምቢተኝነት አድጓል።

ዛሬ ከዚህ በፊት ያልተሞከሩ የትግል ስልቶች ተግባራዊ እየሆኑ ነው። በዚህ ረገድ የሙስሊም ኢትዮጵያዊያን የተቀናጁ ርምጃዎች በአርዓያነት የሚጠቀሱና የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ድጋፍ የሚሹ ናቸው። እነዚህ የሕዝባዊ እምቢተኝነት ተግባራት የእምነት አጥር ሳይለያየን ፍትህ የተጠማን ዜጎች ሁሉ ልንተገብራቸው የሚገቡ ናቸው።

ለምሳሌ፣ ተንቀሳቃሽ ስልኮችን በተወሰኑ ቀናት መዝጋት በተቀናጀ ሁኔታ ከተደረገ ከፍተኛ ውጤት ሊያመጣ የሚችል፤ በሙስሊም ወገኖቻችን ግንባር ቀደም መሪነትና አስተባባሪነት ተሞክሮ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል መሆኑ የታየ አንድ የትግል ስልት ነው።

በአሁኑ ወቅት ተግባራዊ በመደረግ ላይ ያለው ሣንቲሞችን የመሰብሰብ ዘመቻም ሌላ ከዚህ በፊት ያልተሞከረ፤ በተጨማሪ እርምጃዎች ከታገዘ ህወሓት መራሹ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሀገሪቱን ገንዘብ መቆጣጠር የማይችልበት ደረጃ ላይ ሊያደርስ የሚችል ጉልበት ያለው ስልት ነው። ውሳኔው ሣንቲሞችን ብቻ ሳይሆን የወረቀት ኖቶችንም ሲያካትት በዝውውር ላይ የሚኖረውን ገንዘብ ብዛት የሚቆጣጠረው ህወሓት ሳይሆን በደል ያንገሸገሸው ሕዝብ ይሆናል። በባንኮች ያለ ተቀማጭ ገንዘብ በማውጣትም የህወሓት የፋይናንስ ተቋማትን ማሽመድመድ ሌላ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል ስልት ነው። በእነዚህ እርምጃዎች የተለማመደ ሕዝብም ወደ ግዢ እቀባ፤ ለተወሰኑ ቀናት ከቤት አለመውጣት ብሎም "ግብር አልከፍልም" ወደማለት ሊሸጋገር ይችላል።

እንዲህ ዓይነቱ ስልቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ግን የመላው ሕዝብ ተሳትፎ እና የተቀናጀ አሠራርን ይፈልጋል። ለምሳሌ፣ ሰብስቡ ሲባል መሰብሰብን፤ በትኑ ሲባል መበተን ይጠይቃል። እንዲህ ዓይነት የተቀናጁ የጋራ እርምጃዎች በአምባገኑ የህወሓት አገዛዝ ላይ ከሚያደርሱት ጥቃት በተጨማሪ በኢትዮጵያዊያን መካከል ያለውን መግባባት ያጠናክራሉ። እንዲህ ዓይነት የተቀናጁ የጋራ እርምጃዎች በማኅበረሰብ ቡድኖች መካከል አዎንታዊ መስተጋብር ለመፍጠር የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ነው።

አሁን አገራችን የምትገኝበት ሁኔታ በጥሞና ሲጤን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይነጋገር መግባባት፣ እርስ በርሱ መናበብ የሚችልበት ደረጃ ላይ እየደረሰ መሆኑ መረዳት ይቻላል። ይህ ስነልቦናዊ ዝግጅት ደረጃ በደረጃ ጠንከር ያሉ እርምጃዎችን ለመውሰድ ያዘጋጀናል።

በማናቸውም የጋራ እርምጃዎች ለግል ጥቅሞቻቸው ቅድሚያ የሚሰጡ፤ ራሳቸው "ብልጥ" አድርገው በማየት በተፈጠረው ሁኔታ መጠቀም የሚፈልጉ፤ በሌላው ድካም ለማትረፍ የሚሯሯጡ ሰዎች መኖራቸው የማይቀር ነው። ህወሓት ለሃያ አራት ዓመታት ኮትኩቶ ያሳደገው የአድርባይነት ባህልም ሌላው እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል መገመት ቀላል ነው። ድህነት ደግሞ በገዢዎች ላይ ጨክነን የመነሳት አቅማችንን እንደሚያዳክም የታወቀ ነው። ሆኖም ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፊቱ የቀረበለት ምርጫ "ባርነት ወይስ ነፃነት" መሆኑን የተገነዘበበት ጊዜ ላይ ደርሰናል።

በዚህም ምክንያት ለህወሓት ባርነት ከመገዛት ነፃነትን የሚመርጥ ዜጋ ሁሉ ዋጋ ለመክፈል መዘጋጀት ይኖርበታል። ለሁላችንም የሚሆን የትግል ዘርፍ መኖሩ የሕዝቡን ተሳትፎ ከፍ ያደርገዋል። የሁለገብ ትግል ስትራቴጂ ጥቅሙም እዚህ ላይ ነው። ማንም የማንም ነፃ አውጭ አይደለም። ሁላችንም ተባብረን ሁላችንንም ነፃ እናወጣለን።

አርበኞች ግንቦት 7፡ የአንድነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ "ትግላችን ዘርፈ ብዙ ነው፤ ተግባራዊ ትግል የሚደረገውን በሁሉም ቦታዎች ነው፤ እርጃዎቻችን እናቀናጅ፤ ወቅቱ የተግባራዊ ትግል ነው" ይላል።

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!!**

---

## ማእከላዊ እስር ቤት ተቃዋሚዎችን ሊቀላቀሉ ሲሉ ተያዙ በተባሉ ሰዎች ተጨናንቋል

ካለፉት 8 ወራት ጀምሮ በማእከላዊ እስር ቤት ወይም ህዝብ የወያኔ ቄራ እያለ በሚጠራዉ እስር ቤት ውስጥ የታሰሩት እስረኞች አብዛኞቹ አርበኞች ግንቦት7 ትን ሊቀላቀሉ ሲሉ ተይዘዋል የሚል ክስ ሲመሰረትባቸው እስካሁን ድረስ ክስ ያልተመሰረተባቸው በርካታ እስረኞች እንደሚገኙ ምንጮች ገልጸዋል። የሰማያዊ ፓርቲ የአመራር አባላት ከሆኑት ብርሃኑ ተክለያሬድ፣ ፍቅረማርያም አስማማውና እየሩሳሌም ተስፋው እንዲሁም የቀድሞው የአንድነት አመራር አባል የነበረው መሳይ ትኩና ሶስት የድርጅቱ አባላት፣ ከአብርሃ ጅራ፣ መተማ፣ ጎንደር፣ ባህርዳር እና አዲስ አበባ የመጡ በርካታ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን በማእከላዊ ታስረዋል።በአንዳንዶቹ ላይ ለአርበኞች ግንቦት7 ሰዎችን ሲመለምሉና ወደ ኤርትራ ሲልኩ ነበር የሚል ክስ ሲቀርብባቸው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በአዲስ አበባ እና በክልል ከተሞች የአርበኞች ግንቦት7 ትን መረብ (ኔትወርክ) ሲዘረጉ ነበር የሚል ክስ ቀርቦባቸዋል። ምንጮች እንደሚሉትአንዳንድ ወታደራዊ ሃላፊዎችም ታስረው ከሚገኙት መካከል ናቸው። ቀድሞ ብሎ ከጋምቤላ ተይዘው የመጡት እስረኞች በማእከላዊ ከፍተኛውን ቁጥር ይዘው የነበሩ ቢሆንም፣ በአሁኑ ሰአት ከአርበኞች ግንቦት7 ጋር በተያያዘ እየታፈሰ የሚገቡት ሰዎች ማእከላዊን አጣበውታል። የአየር ሃይ ል አባላት የሆኑት ዳንኤል ግርማ፣ ማስረሻ ሰጠኝ፣ ገዛሃኝ ደረሰ እና ብሩክ አጥናባቸው በማእከላዊ እስር ቤት ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ ተደብድበዋል። ስማቸውን እስካሁን በትክክል ለማወቅ ባይቻልም፣ ከአብርሃ ጅራ አካባቢ የተያዙት አንድ የኢህአዴግ ወታደር አመራር ከፍተኛ ድብደባ ተፈጽሞበት ማእከላዊ ታስሯል። በቅርቡ ከዚሁ አካባቢ አርበኞች ግንቦት7ትን መንገድ መርተው ወደከተማ አስገብተዋል ተብለው የተያዙት ወደ ማእከላዊ ተዛውረዋል። ቀድሞ ብሎ የአብርሃ ጅራ የአንድነት ፓርቲ አመራር አባላት አንጋው ተገኝ፣ አባይ ዘውዱና ሌሎችም ተመሳሳይ የሽብር ክስ ተመስርቶባቸዋል። መንግስት በሰሜን የአገሪቱ ክፍል ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰራዊት አሰማርቶ እንደሚገኝ መዘገባችን ይታወቃል። አሁን እንደ አዲስ የተጧጧፈው ዘመቻም በአካባቢው የሚታየው ውጥረት የፈጠረው ሊሆን እንደሚችል ምንጮች ያክላሉ።ታዋቂው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ የቀድሞው የአንድነት አመራሪዎች አንዱአለም አራጌና ናትናኤል መኮንን፣ የመኢዴፓው ክንፈሚካኤል ደበበ ( አበበ ቀስቶ)፣ የሽዋስ አሰፋ፣ ሃብታሙ አያሌው፣ ዳንኤል ሽበሺ እና ሌሎችም ታዋቂ ፖለቲከኞች ከግንቦት7 ጋር ሲሰሩ ተገኝተዋል የሚል ክስ ተመስርቶባቸው በእስር ላይ መሆናቸው ይታወቃል።

---

## ኢ/ር ይልቃል ከአገር እንዳይወጡ የተከለከሉበትን ምክንያት የሚነግራቸው ማጣታቸው ተዘገበ

የሰማያዊ ፓርቲ ሊ/መንበር ኢ/ር ይልቃል ጌትነት ወደ አሜሪካ ሊያደርጉት የነበረው ጉዞ በደህንነት ሰዎች እንዲሰረዝ ከተደረገ በሁዋላ፣ እስካሁን ድረስ ምክንያቱን የሚነግራቸው አካል መጥፋቱን ሊ/መንበሩ ለነገረ ኢትዮጵያ ተናግረዋል። የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ መስሪያ ቤት "ፓስፖርቱ እኛ ጋር አልደረሰም። ቆይተው ደውለው ይጠይቁ" ብለው ስልክ እንደሰጧቸው የገለጹት ኢ/ር ይልቃል፣ ይህም ሆን ተብሎ ጉዞውን ለማጓተት የተደረገ ነው ብለዋል። "ይህን ሁሉ የሚያደርጉት አገር የማስተዳደር ብቃት ስለሌላቸው፣ የፖለቲከኛን እንቅስቃሴ በማጓተትና በማገድ የተፈጠረባቸውን ስጋት የሚቀርፉ ስለሚመስላቸው ነው። ከአቅመ ቢስነታቸው የመነጨ ነው" ሲሉ ለጋዜጣው ተናግረዋል። ኢ/ር ይልቃል ጌትነት ሰማያዊ ፓርቲ በውጭ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ያለው ተቀባይነት ገዢውን ፓርቲ እንዳስፈራውም አክለዋል።

---

# ዘመናዊ ባሪያ ፍንገላ በኢትዮጵያ

ነፃነት ዘለቀ (ከአዲስ አበባ) ክፍል 2 የመጨረሻ ክፍል

ነገሩ እንዲህ ነው። የነሚሚና አዜብም ሆነ የሌሎቹ በሥራ አስቀጣሪነት ፈቃድ አውጥተው በሕዝብ የሚነግዱ ድርጅቶች ሠራተኞችን "ሥራ እናስቀጥራችኋለን" በሚል በየሙያ ዘርፉ ይመዘግባሉ፤ ይመለምላሉ። የተወሰነ የአጭር ጊዜ ሥልጠናም ሳይሰጡ አይቀሩም። በተለይ የጽዳትና የጥበቃ ሠራተኞችን፣ የጉልበት ሥራና መሰል አገልግሎት የሚሰጡ ሠራተኞችን የሚፈልጉ መሥሪያ ቤቶች ወደነዚህ ባሪያ ፈንጋዮች ዘንድ በመሄድ የሚፈልጉትን የሠራተኛ ዓይነት እንደፍላጎታቸው መርጠው ይወስዳሉ። ቀጣሪዎች፣ ደሞዝ ከፋዮች፣ አስጠንቃቂዎች፣ ከሥራ አሰናባቾች፣ ... እነዚሁ አስቀጣሪ ድርጅቶች ናቸው። ሰዎቹን ወስዶ የሚያሠራቸው ድርጅት ግንኙነቱ ከ"ባሪያዎቹ" ጋር ሣይሆን ከአስቀጣዎቹ ድርጅቶች ጋር ነው። ይህ ዘመናዊ የባሪያ ፍንገላ አሠራር በሀገር ውስጥ ብቻ የተወሰነ አይደለም። መንግሥት የፈቀደላቸው የሚባሉ ወደውጪ ሀገራት በተለይም ወደዐረቡ ዓለም የቤትና የጉልበት ሠራተኞችን የሚልኩ አሉ። የሚያስከፍሉት ገንዘብ አንጀትን ይመዘምዛል አሉ። የነሱን የመጓጓዣና የደላላ ወጪ ለመክፈል የሚፈጀው ጊዜ የወላጅንና የተደጓሚ ቤተሰብን አንጀት በርሀብ ያነጥፋል። በዚያ ላይ አንዴ ከላኳቸው በኋላ ቢቀቀሉ ቢገነተሩ መብታቸውን ለማስከበር ዘወር ብለው አያዩዋቸውም ይባላል። አበሻ እንዲህ ሆዳምና ጨካኝ የሆንነው ግን ከመቼ ጀምሮ ይሆን እባካችሁ? የነሚሚ ጦስ ድንበር ዘለል ነው። ገንዘብ ባለበት ወያኔ አለ። ንግድ ባለበት - እዚህ በተጨባጭ እንደምናየው ሰውም ይሸጥ መሬትና ተንቀሣቃሽ ንብረትም ይሸጥ - ወያኔና የሙስና እናት የምትባለዋ አዜብ አይጠፉም። ይቺ የመርገም ፍሬ ሴትማ የጉልት ሴቶችን ሳይቀር በሽርክና አስገቡኝ ከማለት አትመለስም ይባላል - ፈጣሪን ምን ብንበድለው ይሆን ግን ለዚህ ለወሬ እንኳን ለማይመች መከራና ስቃይ የዳረገን? ይህችን ሴት ባሰብኩ ቁጥር አንዳርጋቸው ጽጌ(አንዱ) የተናገራት cringe የምትል ቃል ትዝ ትለኛለች፤ አዎ፣ ምን የመሰለ ድንቅ ታሪክ ያለን ሕዝብ ይቺን በመሰለች ሴት ስንታመስ በርግጥም መሸማቀቅ ሲያንሰን ነው። ለማንኛውም በነዚህ ሴቶችና ተባባሪዎቻቸው መሬት መሸከም የሚከብዳት ግዙፍ ግፍና በደል እየተፈጸመ ነው። ከፍ ሲል የጠቀስኩላችሁ የሀገር ውስጥ ባሪያ ፍንገላ የደመወዝና የጥቅማጥቅም ነገር ሲነሳ ነው ግፉ ቁልጭ ብሎ የሚታየን። በጥቂቱ እንየው፡-

እኔን የቀጠረኝ የግል ድርጅት ከነዚሁ የድሃን ደም መጣጮች ነው የጽዳትና የጥበቃ ሠራተኞቹን የተኮናተረው። እነዚህ ምሥኪን ሠራተኞች ደሞዛቸውን የሚያገኙት ከኛ ድርጅት ሣይሆን ከቀጠራቸው አስቀጣሪ ድርጅት ከነሚሚ ወይም ከነአዜብና መሰሎቻቸው ነው - አንዳች ሳይለፉ በድሃው ጉልበት የማይነጥፍ የነዳጅ ጉድጓድ የቆፈሩ ዘራፊዎች። የኔ መሥሪያ ቤት ለአንድ ጥበቃ ብር 1100 (አንድ ሺህ አንድ መቶ ብር) ለቀጣሪ-አስቀጣሪው ድርጅት ይከፍላል። አስቀጣው ድርጅት ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ግማሹን ለሥራ ማስኬጃ ይቀነድብለትና ግማሹን ብር 550 ለሠራተኛው በየወሩ ይከፍለዋል - በመረጃ የተደገፈ ወሬ ነው የምነግርህ። ይህ ሠራተኛ የኛ ድርጅት ቋሚ ቅጥር ቢሆን ኖሮ አንደኛ ደሞዙ ከዚህ አሁን ከሚከፈለው ሻል ሊል ይችል ነበር - የኛ ድርጅት ጭንቅላት የለውም እንጂ ቢኖረው ኖሮ ማለቴ ነው። ሁለተኛ የሕክምና ዋስትና ይኖረው ነበር። ሦስተኛ የጡረታ ዋስትና(Provident Fund) ይቆረጥለት ነበር። አራተኛ የሥራ ዋስትናው አሁን ካለበት ሁኔታ በጣም የተሻለ ይሆንለት ነበር(አሁን እንደ ዕቃ ነው፤መናገር፣ ማጉረምረም፣ መውቀስ፣ ምናምኒት አይችልም - ወዲያውኑ ይባረራል።) እኛ ቢያንስ በግል ስንገናኝ የማጉረምረም መብታችን የተጠበቀ ነው። እነዚህ በወር 550 ብር የሚከፈላቸው የጥበቃና ጽዳት ሠራተኞች ባለፈው ጦማሬ የገለጽኩላችሁን የአዲስ አበባ የኑሮ ውድነት እንዴት ሊቋቋሙት እንደሚችሉ እንግዲህ አስቡት። የዱሮ ባሪያ ደረጃውን የጠበቀ አይሆን እንደሆነ እንጂ ቢያንስ በሕይወት ሊያኖረውና ሥራውን በአግባቡ እንዲሠራ ሊያደርገው የሚችል ምግብ ይሰጠው ነበር። የዘመናዊ ባርነት ሰለባዎች ግን የላባቸውን ውጤት የሚበላው ሌላ በመሆኑ ለትራንስፖርትም በማይበቃ ገንዘብ ጉልበታቸው ይበዘበዛል፤ ሥራ አላቸው እንዲባሉ ግን ውለው ይገባሉ። እነዚህ አስቀጣሪ ድርጅቶች በመያዶችና በዓለም አቀፍ ድርጅቶችም ያስቀጥራሉ። ከዚያም አካባቢ እንደሰማሁት ባሪያ ፈንጋዮቹ በብዙ ሺዎች ይቀበሉና ለሁለተኛ ዙር ተቀጣሪው ሠራተኛ የሚያቀምሱት በቡና ሥኒ ነው አሉ። ሰው ሌላ አማራጭ ስለሚያጣ በግዱ ወደነዚህ ድርጅቶች ይሄዳል። ወደ አሠሪዎቹ ድርጅቶች ሄዶ መቀጠር እንዳይችል እነዚህ የኔን ቀጣሪ ድርጅት መሰል ድርጅቶች ኃላፊነትን ይሸሻሉ። ከሠራተኛ ቁጥጥር፣ ከጥቅማጥቅም፣ ከሠራተኛና አሠሪ የክስ ውጣ ውረድና ከመሳሰለው የተገላገሉ እየመሰላቸው በእጅ አዙር የሰውን ጉልበት ይበዝብዛሉ። ግፍ በየዓይነቱ የሚናኝባት ብርቅዬ ሀገር አለችን።

መፍትሔው ምን ይሁን ትላላችሁ? መፍትሔው እንደኔ የአስተሳሰብ ለውጥ ነው። የወያኔ ዓይነቱ ትውልድን አምካኝ የትምህርት ሥርዓት ሣይሆን ሥጋንና ነፍስን የሚያስታርቅ መንፈሣዊና ዓለማዊ ትምህርት ያስፈልገናል። በኢትዮጵያችን የሞራል ዕሤቶች ታጥበው ገድል ከገቡ በኋላ ይመስለኛል ይህ ዓይነቱ የጅብ ባሕርይ ወደ ሰዎች የተጋባው። እንጂ አምስት መቶ ብር ለውሻው የወር ባጀት እንደማይሆን የሚረዳ አንድ ሀብታም "ኢትዮጵያዊ" ዜጋ እንዴት አንድ መሰል ዜጋውን በዚህ ደሞዝ ያሠራል? ምን ዓይነት ደደብነት ነው? በተዘዋዋሪ ቀጥሮ የሚያሠራቸው ድርጅትስ ቢሆን ምናለበት ይህን ችግር ተገንዝቦ ራሱ በቀጥታ ቢቀጥራቸውና ያን አላግባብ የሚመዘበር ገንዘብ ለነሱ ቢያደርገው? ምን ዓይነት ሁልአቀፍ የሆነ የአስተሳሰብ ስንኩልነት ነው እየታዘብን የምንገኘው? አእምሮ ወዴት ገባ? ወዴት ሸፍቶ ይሆን? እዚች ላይ ትንሽ እንጸልይ መሰለኝ፡- " አቤቱ የሰማዩ አባታችን እግዚአብሔር ሆይ፣ በሞራ የተሸፈነ ኅሊናችንን ግለጥልንና እውነቱን እንድናይ አድርገን! ለሰዎችም እንድናዝን የርህራሄና የመተሳሰብን መንፈስ በላያችን አሳድርልን። ለይቶልን ሳንጠፋ ጭል ጭል በምትለዋ እስትንፋሳችን ላይ ሞልቶ ከሚፈሰው የማያልቅ ቸርነትህ ላክልንና ወደየልቦናችን ተመልሰን እንድንተዛዘን፣ እንድንፈቃቀድም አድርገን። ጨርሰን ሳንጠፋብህ በመሀከላችን ገብተው የሚያበጣብጡንን የፍቅረ ንዋይና የአምልኮተ ንዋይን መንፈስ፣ የዘረኝነትና የሙስናን ደዌያት አስወግድልን። አሜን።"

ችግርን ከማውራት የምገላገልበትን ጊዜ በጣም ናፍቄያለሁ። ሁልጊዜ ስለችግር ስለማወራ ራሴኑ ጭምር እንደችግር ማየት ከጀመርኩ ቆይቻለሁ። ከዚህ ቅኝት ለመውጣት ወደፊት ትልቅ ትግል ሳይጠብቀኝ አይቀርም።

ወደ ሌላ ችግር። ሰሞኑን የወያኔው መንግሥት 37ሺህ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በዕጣ ማከፋፈሉ ይታወሳል። ዕጣ አወጣጡ ራሱ ችግር እንዳለበት ሰምቻለሁ። እመለስበታለሁ።

ዕጣ ያልወጣላቸው ሰዎች "እንኳንስ ዕጣ አልደረሰኝ!" እያሉ የሚደሰቱበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ምክንያቱም አስቀድሞ የሚከፈለው ገንዘብ ከየት መጥቶ ይከፈል? ዕጣ የደረሳቸው አንዳንድ ጓደኞቼ "ምን ቅብጥ አድርጎኝ ነው የተመዘገብኩት"እያሉ ሲያማርሩ ታዝቤያለሁ። ምዝገባው የተካሄደው ቀደም ሲል ነው። ሰው ደግሞ ሲመዘገብ አንዳንዱ ለደራ ነው - ዕድሉን ለማየት። አንዳንዱ - እንዲያውም ብዙው ከመኖሪያ ቤት ችግሩ አንጻር ነው። አንዳንዱ ለትርፍ ነው - ቤት እያለው ግን ኮንዶምንየሙን ሸጦ ትርፍ ለማግኘት። አቤት የመጥፎ ጠባያችን አበዛዙ! ስንትና ስንት ሌላ አማራጭ እያለው ለዚች የአንድና የሁለት ክፍል ጎጆ ከድሃው ጋር ሙሉ ቀን ተሠልፎ የድሃውን ዕድል የሚያሰነካክል ሀብታም ታያለህ። በሚስቱም በልጁም በዘመዱም ስም ብዙ ቤት እያለው ለዚች ትንሽዬ ነገር የድሆችን ዕድል ሲያጨነግፍ የምታየው ገብጋባ ሰው አለ። ብዙ ችግር እኮ ነው ጓዙን ጠቅልሎ ወደሀገራችን የገባው። ለሰው ደግ መመኘትና "ይህ ለኔ በቂ ነው፤ ይህም የሌላቸው አሉና ለነሱ ይሁን" ብሎ ማሰብ ቀርቷል። እናላችሁ አዳሜ ዕድሏን ለመፈተንና "ከዚህ ወይ ከዚያ በማገኘው ገንዘብ አሟልቼ ቅድሚያ ክፍያውን እከፍላለሁ፣ ከዚያም እኔ በአነስተኛ ገንዘብ እከራይና ቤቱን በትልቅ ዋጋ አከራይቼ ወይ ሸጬ በማገኘው ትርፍ ዕዳየን በቶሎ አጠናቅቃለሁ" ብላ አስባ ስታበቃ አሁን ዕጣው ሲወጣላት ጊዜ ምኑን ከምን ታ'ርገው? ለምሳሌ በምዝገባው ወቅት 60ሺህ ብር ገደማ ተብሎ የተነገረው የባለ ሁለት መኝታ ቤት ኮንዶምንየም የቅድሚያ ክፍያ አሁን በወቅቱ የገንዘብ ምንዛሬ ተሻሽሎ ከ80ሺህ ብር በላይ ሆኗል። አንዱ ጓደኛየ የዚሁ ቤት ዕጣ ደርሶት ዕጣው ከወጣበት ዕለት ጀምሮ የሌት እንቅልፉንና የቀን ሰላሙን አጥቷል። የርሱ ደሞዝ ከዕለታዊ መጠነኛ ኑሮ አያልፍም። በዕቁብም ሆነ ወደፊት የሚከፈል ተብሎ በብድር መልክ ከሰው ማግኘት የሚታሰብ አይደለም - ከመነሻው ድሃን አምኖ የሚያበድረውም የለም። ብድርና ቁጠባ ቢል ያጠራቀመው በጣም ጥቂት ነው። ፒኤፍ ቢጠይቅ እሺ አልተባለም - ቢፈቀድለት እንኳን አይሞላለትም። ሥራውን ለቅቆ ፒኤፉን እንዳይወስድ በዛሬ ጊዜ በመከራ የሚገኝና በዘመድ አዝማድ በተቆላለፈ ማኅበረሰብ ውስጥ ሌላ ሥራ መፈለጉ መድሓኒት የሌለው ትልቅ ራስ ምታት ነው። እናም እንዲሁ እየዋተተ አለ። በዚህ ሁኔታ የሚቸገሩ ብዙዎች ናቸው። ይህ አጋጣሚ ደስታ ሀዘንን ሲወልድ ያየሁበት ልዩ አጋጣሚ ነው። በነገራችን ላይ ይህን የኮንዶምንየም ቅድሚያ ክፍያ በሴከንድ ውስጥ የሚከፍሉ ግን ባለአነስተኛ ደሞዝተኞች አሉ። እነዚህም የሙስናው ሞተር አሽከርካሪዎችና ልየ ልየ የጎን ገቢ ያላቸው ናቸው። ሙስና ካለ እንኳንስ ኮንዶምኒየም አሮጵላንም ይገዛል። ይብላኝ ዙሪያ ገባው ለጨለመበት ተራው የመንግሥትና የግል ድርጅቶች ሠራተኛ! ይብላኝ በረንዳዎችን ሙጥኝ ብሎ ለሚገኘው በመቶ ሺዎች ለሚገመተው ዜጋ። ስለወቅቱ የሥራ አያያዝ ሁኔታ ግን ትንሽ ላውራችሁ።

በዛሬ ጊዜ ይገርማችኋል ወርቅ የሆነ የሥራ ችሎታና ወርቅ የሆነ ጠባይ ቢኖርህ ሰው የሚቀጥርህ ዘርህን ጠይቆ ነው። የሀገራችን ሠራተኛ ያሣዝናችኋል። በየጠላና አረቂ ቤቱ ስዘዋወር የምሰማው የዘረኝነት መዘዝ የፈጠረው ብልሹ አሠራር ዕበድ ዕበድ ነው የሚለኝ። ምን የመሰለ የግምበኝነትና የአናፂነት ሙያ እያለው ትግሬ ወይም ኦሮሞ ባለመሆኑ ብቻ የሚቀጥረው አጥቶ ሲንቀዋለልና በየቁንድፍት ቤቱ ጉበቱን ሲያቃጥል በኃያሉ አምላክ ፊት ሣይቀር የምሰጥለት የሀገራችን የወቅቱ ነቀርሣ ነው። .... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ጋምቤላ ፊት ለፉቷ ላይ ሌላ የጎሳ ግጭት ተደቅኖባታል ሲሉ የጋምቤላ ኒሎትስ አንድነት ንቅናቄ አደራጅ ተናገሩ

የጋምቤላ ኒሎትስ አንድነት ንቅናቄ መስራችና አደራጅ የሆኑት አቶ አኮክ ከኢትዮጵያ ሳቴላይት ቴሌቪዥንና ሬድዮ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ እንደገለጹት የህዝባዊ ወያን ሃርነት ትግራይ መንግስት በአካባቢው ያለውን መሬት ሙሉ በሙሉ ጠቅልሎ ለመውሰድ ባለው ፍላጎትበአኝዋኮችና በኑወር ብሄረሰቦች መካከል ግጭት ለመፍጠር እየተንቀሳቀሰ ነው። ኑወሮችን በጦር መሳሪያ ከማስታጠቅ ጀምሮ ከደቡብ ሱዳን የሚፈናቀሉ ኑዌሮች በአኝዋኮች፣ መዠንገሮችና ሌሎች ብሄረሰቦች መካከል እንዲሰፍሩ በማድረግ እስከዛሬ የነበረውን የህዝብ አሰፋፈር በመቀየር አዲስ ግጭት ለምፍጠር ይቀሳቀል በማለት አቶ አኮክ ክስ አቅርበዋል።

በመጋቢት ወር 2 አኝዋኮች መገደላቸውንና 3 ደግሞ መቁሰላቸውን እንዲሁም በርካታ ሴቶች እና ህጻናት ከ ፒንዩዶ የስደቶች ካምፕ ታፍነው መወሰዳቸውን ፣ በየካቲት ወር ደግሞ 2 ህጻናት ታፍነው ሲወሰዱ፣ አንድ የአኝዋክ አርሶ አደር ደግሞ ተገድሏል። በኩትቡዲ ፒንዩዶም እንዲሁ 4 አኝዋክ ህጻናት ታፍነው ሲወሰዱ፣ የኒዩም መንደር አዣዥ ኦጉልም እንዲሁ ተገድለዋል። ከአሁን በፊት በተቋቋሙት ቦንጋ፣ ዲማ፣ ፒኑዩዶ እና አኩላ ወይም ኢታንግ የሰፈራ ጣቢያዎች የገቡት የደቡብ ሱዳን ስደተኞች አልበቃ ብሎ በአኝዋክ፣ መዠንገር፣ ኦፖ እና ኮሞ ጎሳዎች መሬቶች ላይ ቾላን፣ ፖኮንግ፣ ጃዊ፣ ኦቾም፣ ኮቦን፣ ካራሚ የተባሉ አዳዲስ የሰፈራጣቢያዎች መቋቋማቸው ሆን ተብሎ ግጭት ለመፍጠር መሆኑንና ምልክቶችም በመታየት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ዋናው አላማው በክልሉ የሚታየውን መሬት ለመቀራመት መሆኑን የሚገልጹት አቶ አኮክ ፣ ሁለቱ ብሄረሰቦች በሚጋጩበት ጊዜ ተጠቃሚዎቹ መሬቱን የሚዘርፉት የህወሃት ሰዎች ናቸው ብለዋል። በቅርቡ ከ80 በላይ አኝዋኮችና 45 መዠንገሮች በማእከላዊ እስር ቤት ታስረው እንደሚገኙ፣ የቀድሞውን የክልሉን መሪ አቶ አኬሎ አኳይን ጨምሮ ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ በርካታ አኝዋኮች ከደቡብ ሱዳን ጁባ ወደ ኢትዮጵያ ተላልፈው መሰጠታቸውን ገልጸዋል። በክልሉ እየደረሰ ያለው ጭፍጨፋ በአጼ ሃይለስላሴ እና ደርግ ከነበረው ጋር ሲተያይ አስከፊ መሆኑን የገለጹት ሃላፊው፣ በዚህ ቀጠለ ለዘመናት መስዋትነት የከፈልንላትን አገራችንን እንዳናጣት ሲሉ አስጠንቅቀዋል።

እነ ብርሃኑ ተክለያሬድ ፍርድ ቤት ቀረቡ በቅርቡ በቁጥጥር ስር የዋሉትእና በማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ በእስር ላይ የሚገኙት ብርሃኑ ተክለ ያሬድ፣ ፍቅረማሪያም አስማማውና እየሩሳሌም ተስፋው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አራዳ ፍርድ ችሎት ቀርበው ተጨማሪ የ28 ቀናት ቀጠሮ ተጠይቆባቸዋል። ተጠርጣሪዎቹ ችሎት ከመግባታቸው በፊት በፈገግታ በፍርድ ቤት ቅጥር ግቢ የነበሩትን ቤተሰቦቻቸውን፣ ጓደኞቻቸውንና ወዳጆቻቸውን ሰላም ሲሉ መታየታቸውን ጋዜጠኛ ኤልያስ ገብሩ በፌስ ቡክ ገጹ ዘግቧል። ጠበቃ ዳዊት ከችሎት በኋላ ለጋዜጠኞች እንደተናገሩት መርማሪ ፖሊሶች ምርመራ አለመጨረሳቸውን፣ ተጠርጣሪዎች ካልተያዙ ግብረ አበሮቻቸው ጋር ግንኙነት እንደነበራቸውና ይሄንንም በማጣራት ላይ እንደሚገኙ፣ የቴክኒክ መረጃዎች (የኮምፒውተር፣ የኢንተርኔት፣ የስልክና የፌስ ቡክ) እንደሚቀራቸው፣ ለሽብር ተግባር ብር ሲቀበሉ እና ሲልኩ የነበረውን የባንክ ቤት መረጃ እየተከታተሉ መሆናቸውና ቢለቀቁ መረጃዎችን ሊያጠፉ ስለሚችሉ የተጨማሪ የ28 ቀናት ቀጠሮ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል። ጠበቃ ዳዊት "መርማሪ ፖሊስ ይቀሩናል ሲል ለፍርድ ቤቱ ያቀረባቸው መረጃዎች ከተጠርጣሪዎቹ ቁጥጥር ውጪ ሆነው በቃላሉ የሚገኙ፣ ፖሊስ የኮምፒውተር፣ የኢንተርኔት፣ የስልክና የፌስ ቡክ መረጃዎችን እስከአሁን ሊያገናቸው ይችል እንደነበረ፣ ከባንክ የሚገኝ መረጃም በአጭር ቀናት ውስጥ የሚገኝ መሆኑን፣ ግብረ አበሮች አሉ ከተባለም ግብረአበሮች የሚያዙት ተጠርጣሪዎችን በመያዝ አለመሆኑና ተጠርጣሪዎቹ ቢለቀቁም የተለየ ነገር እንደማይመጣ ተከራክረዋል።

መርማሪ ፖሊስም "የጦር መሳሪያ ተይዟል። ተጠርጣሪዎቹ በህቡዕ ነው የሚንቀሳቀሱት። ከእስር ቢለቀቁ ወደኤርትራ ሰው ወደመመልመል ስራቸው ይመለሳሉ" የሚል ተቃውሞ በማሰማት፣ የጦር መሳሪያ የታጠቀ የሰው ምስል ለችሎት ማሳየቱንና መሳሪያ የያዘው ግለሰብ ማን እንደሆነ በግልጽ እንደማይታይ ጋዜጠኛ ኤልያስ ዘግቧል። ፍቅረማርያም እና እየሩሳሌምም ቃላቸውን፣ የፌስ ቡክና ሌሎች መረጃዎችን በምርመራ ወቅት ለፖሊስ መስጠታቸውን፣ መሳሪያ ከተባለው ነገር ጋር የሚያገናኛቸው ነገር አለመኖሩንና ይሄም በግልጽ እንደሚታወቅ በመግለጽ "መረጃዎች ካሉ ክስ ይመስረትብን ካልሆነ ከእስር እንለቀቅ" የሚል ሀሳባቸውን ለችሎቱ አቅርበዋል። ሁለቱ ተጠርጣሪዎች የ28 ቀናት የጊዜ ቀጠሮ ከተጠየቀባቸው በኋላ ብርሃኑ ተክለያሬድ ወደ ችሎት መግባቱን፣ መርማሪ ፖሊሱ፣ ብርሃኑ ላይም "የጦር መሳሪያ ተገኝቷል" የሚለውን ቃል ሳይደግም በሁለቱ ተጠርጣሪዎች ላይ ያረቀበውን ሀሳብ ለችሎቱ ማስረዳቱን ጠበቃ ዳዊት ተናግረዋል።

ወጣት ብርሃኑ በበኩሉ "ቃላችንን ለፖሊስና ለፍርድ ቤቱ ሰጥተናል። የቀረ ነገር የለም። የእስር ሁኔታችን ከህግ አግባብ ውጪ ነው። "ጨለማ ክፍል" በሚባለው እስር ቤት መብራት 24 ሰዓት ይበራል። እኔ የዓይን ችግር አለብኝ። በቀን ለ15 ደቂቃ ብቻ ነው ከታሰርኩበት ክፍል ወደ ደጅ የምወጣው። ቤተሰብና የህግ ጠበቃ ማግኘት አልቻልኩም። ከጠበቃ ጋር ሳልማከር ነው ቃሌን ለፖሊስ የሰጠሁት። የመብት ጥሰት አለ። ቤተሰቦቻችንን፣ ጠበቃና ጠያቂዎቻችንን መግኘት ይፈቀድልን። ሌሎች ከእኔ ጋር የታሰሩ እስረኞች ግን ቤተሰቦቻቸው ሲመጡ ለጥየቃ ይወጣሉ። በዚህ ላይ ትዕዛዝ ይሰጥበት። መረጃዎች ካሉ ክስ ይመስረትብን ካልሆነ ከእስር እንለቀቅ" ብሏል። የችሎቱ ሴት ዳኛም የተጠርጣሪዎች ሰብዓዊ መብት መጠበቅ እንዳለበት ጠቁመው፣ "ተጠርጣሪዎቹ ከቤተሰብ፣ ከጠበቃ፣ ከሃይማኖት አባቶቻቸውና ከወዳጆቻቸው ጋር እንዲገናኙ" የሚል ትዕዛዝ በቃል ሰጥተው በብርሃኑም ላይ የ28 ቀናት ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮ ፈቅደዋል።

## ቦሌ አዉሮፕላን ማረፊያ የወያኔ የህገ ወጥ ንግድ ማዕከል

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

በስማቸው ተመዝገበው የሚገኙት የንግድ ድርጅቶችም በአዲሱ መመሪያ መሰረት ውል ሳይገቡ በመነገድ ላይ ሲሆኑ የሚከፍሉት ክፍያ ከወቅቱ ጋር የማይመጣጠንና ተቆጣጣሪ የሌለባቸው መሆናቸውን ምንጮች ገልጸዋል። በአዲሱ ውል መሰረት ውል ሳይዋዋሉ ለ5 አመታት ያክል በአውሮፕላን ማረፊያ ውስጥ በመነገድ ላይ ካሉት ድርጅቶች መካከል ለንደን ካፌና ሳተላይት ሬስቶራንት 109.9 ካሬ ቦታ በአመት ብር 138 ሺ 474 አላፋራጅ ትሬዲንግ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ፣ የይዞታ መጠን 631 ካሬ ሜትር፣ አመታዊ ክፍያ በካሬ ሜትር 8 ሺ 100 ብር ላሊበላ ወርቅ ቤት፣ 31.10 ካሬ ሜትር፣ አመታዊ የክፍያ መጠን በካሬ ሜትር 8 ሺ 100 ብር ሲቲ ቢዝነስ ኮምፒዩተር፣ 104 ካሬ ሜትር አመታዊ የክፍያ መጠን በካሬ ሜትር 8 ሺ 100 ብር ድሬ ኢንዱስትሪ ሃ/የተወሰነ የግል ማህበር 54 ካሬ ሜትር አመታዊ የክፍያ መጠን በሄክታር 8 ሺ 100 ህይወት ለማ ትሬዲንግ 31.10 ካሬ ሜትር የክፍያ መጠን በካሬ ሜትር 8 ሺ 100 ብር ሲማት ትሬዲንግ 31.10 ካሬ ሜትር የክፍያ መጠኑ ባከሬ ሜትር8 ሺ 100 ብር ይገኙበታል። በአጠቃላይ አዲስ በወጣው መመሪያ መሰረት ህጋዊ ውል ሳይፈርሙ በመስራት ላይ የሚገኙት ደርጅቶች የ10 አመታት የኪራይ ዋጋ ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ ሲሆን፣ ኤርፖርቶች ድርጅት እስካሁን እርምጃ ለመውሰድ አለመድፈሩን ምንጮች ገልጸዋል።ጉዳዩ በተደጋጋሚ ለድርጅቱ ቢቀርብም ምላሽ መጥፋቱን ምንጮች አክለው ይገልጻሉ። በጉዳዩ ዙሪያ የኢትዮጵያ ኤርፖርት ኢንተርፕራይዝን አስተያየት ለማካተት ያደረግነው ጥረት አልተሳካም።

## በደቡብ ክልል የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈጸሙት ከፍተኛ

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

የቀድሞው የአንድነት ፓርቲ አመራር አቶ ግርማ ሰይፉ በጉራፈርዳ የደረሰው መፈናቀል" አንድ አገር አለን ብለን እንድናስብ ያደርገናል ወይ ሲሉ የቀድሞውን ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ጠይቀዋቸው ነበርአቶ መለስ ዜናዊ አማሮች ተፈናቀሉ እያሉ የሚናገሩት በኢትዮጵያ አንድነት እንታወቅ የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች መሆናቸውን በመግለጽ፣ በአማሮች ላይ ተፈጸመ የሚለውን ክስ አጣጥለውት ነበር ። ድርጊቱ የተፈጸመው በአማራ ክልል እና በደቡብ ክልል መካከልስምምነት ከተደረሰ በሁዋላ ነው ያሉት አቶ መለስ ይሄ በአማራ ወይም በምስራቅ ጎጃም ነዋሪዎች ላይ የተቃጣ ወንጀል አይደለም ሲሉ የተፈጸመውን ድርጊት ተከላክለው ነበርይሁን እንጅ አቶ መለስ ከሞቱ ከ2 አመታት በሁዋላ አቃቢ ህግ" አማሮች ሆን ተብሎ መገደላቸውን፣ ጥቃቱንም የፈጸሙት የወረዳው ባለስልጣናት መሆናቸውን ዘርዝሮ አቅርቧል።

ምንም እንኳ አቃቢ ህግ የወረዳውን ባለስልጣናት ተከታትሎ ለፍርድ ማቅረቡ የሚመሰገን ቢሆንም፣ ትእዛዙን የሰጡት የፌደራል፣ የክልልና የዞን ባለስልጣናት፣ ጥፋቱን ሁሉ በታችኞች ባለስልጣናት ላይ አድርገው ራሳቸውን ከተጠያቂነት ማውጣታቸው ተገቢአለመሆኑን አቶ ተስፋሁን አለምነህ የመኢአድ አመራር ተናግረዋል።አቶ ሽፈራው ሽጉጤ የክልሉ ፕ/ት በነበሩበት ወቅት ያወጡት ህግ ለግጭቱ መንስኤ መሆኑ በወቅቱ ተዘግቧል። .... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )


**የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## በአማራ ክልል ባለሀብቱ እና ነጋዴው ለአባይ ግድብ ማሰሪያ የሚጠበቅበትን ያህል አስተዋጽኦ አላበረከተም ተባለ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአባይ ግድብ ህዝባዊ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ፅሀፊና የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ንጉሡ ጥላሁን ሰሞኑን ከጋዜጠኞች ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ፣ በአራት አመቱ ውስጥ በክልሉ የተሰበሰበው ገንዘብ ስድስት መቶ ሚሊዮን ብር አካባቢ መሆኑን ገልጸው፤ ከዚህ ውስጥ ከ384 ሚሊዮን ብር በላይ ከመንግስት ሰራተኛው የተሰበሰበ መሆኑን ተናግረዋል። በክልሉ የሚገኙ አርሶ አደሮች ፣ ከተለያዩ ነጋዴዎችና ባለሃብቶች በተሻለ መልኩ 57 ሚሊዮን ብር ሲያዋጡ ነጋዴዎችና ባለ ሃብቶች ግን 44 ሚሊዮን ብር ብቻ ማዋጣቸውን ኃላፊው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ተናግረዋል።

በሃገሪቱ ልዩ ልዩ ቦታዎች የገቢ ማሰባሰቢያ መድረኮች ቢዘጋጁም የተጠበቀውን ያህል ገቢ እንዳልተሰበሰበ የገለጹት ኃላፊው፤ ከመጋቢት 24/2007 ዓ.ም ጀምሮ ለስምንት ቀናት በክልሉ ባሉ ከተሞች በተዘጋጀው የቦንድ ግዢ እንቅስቃሴ አጥጋቢ ውጤት አለመገኘቱ አሳሳቢ መሆኑን ተናግረዋል።

"የግድቡን ስራ በመደገፍ ተገቢውን ማድረግ እንዳለብን ብናውቅም የመንግስት ባለስልጣናት በየደረጃው ስራችንን በአግባቡ እንዳንሰራ የሚጥሉብን ተገቢነት የሌለው ግብር ስላማረረን በሁሉም እንቅስቃሴ ለመሳተፍ ይቸግረናል።" ሲሉ ነጋዴዎች ለዘጋቢያችን ገልጸውላታል። በሌላ በኩል በጎንደር፣ በባህርዳርና ደብረታቦር ከተማ የሚኖሩ የመንግስት ሰራተኞች "የግድቡ መሰራት ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚጠቅም ቢሆንም በአራት አመቱ ውስጥ የተሰበሰበው ገንዘብ ሲታይ እዚህ ግባ የማይባል እና አብዛኛው ገንዘብ የተሰበሰበው ከመንግስት ሰራተኛው ጉሮሮ ተነጥቆ መሆኑ ዘላቂነቱን አጠራጣሪ ያደርገዋል።" ብለዋል።

ሰራተኞቹ በአሁኑ ጊዜ በመንግስት ያሰራር ጉድለት ምክንያት በተለይ በመንግስት ሰራተኛውና ዝቅተኛ ነዋሪው እየደረሰ ያለው የኑሮ ውድነት ከጊዜ ወደ ጊዜ ፈታኝ መሆኑ እየታወቀ፤ ገንዘብ አዋጡ በማለት የሁሉም ፈቃድ ሳይኖር በየጊዜው ከደመዎዛቸው መቆረጡ አግባብነት የሌለው መሆኑን ተናግረዋል። "ባሉብን የኑሮ ክብደት ምክንያት ደመዎዛችን እንዲቆረጥ አንፈልግም።" በማለት ፈቃደኛ አለመሆናቸውን የተናገሩ የመንግስት ሰራተኞች ፣ በየምክንያቱ ከደረጃ ዝቅ እንዲሉና በሰበብ አስባቡ ልዩ ልዩ ቅጣት ሲደርስባቸው መታየቱ፤ ሁሉም የመንግስት ሰራተኞች ዝምታን በመምረጥ በኑሮ ውድነት ለመሰቃየት መዳረጋቸውን ገልጸዋል። በግድቡ ስራ ዙሪያ በመጀመሪያ አካባቢ የነበረው የተነሳሽነትና ቁጭት ስሜት ዛሬ እየጠፋ መሆኑን የሚገልጹት አስተያየት ሰጪዎች፣ አሁንም "ግድቡ 42 በመቶ ደርሷል የሚለው መግለጫ ትክክል ለመሆኑ ጥርጣሬ አለን" በማለት የገዢው መንግስት ሁልጊዜም በቁጥር በኩል እውነት አለመናገሩ የተለመደ መሆኑን ይናገራሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ባለፉት አራት አመታት ለአባይ ግድብ ማሰሪያ እስካሁን የተሰበሰበዉ ገንበዘብ የታሰበዉን ያክል አለመሆኑ ታወቀ። እንደ ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች አባባል ከሆነ ይህ ሊሆን የቻለዉ የወያኔ አገዛዝ ሁሉንም ኃይሎች ያሳተፈ ብሔራዊ መግባባት መፍጠር ባለመቻሉ ነዉ። ይናገራሉ።የግድቡ የመሰረት ድንጋይ የተጣለበት 4ኛ ዓመት በዓል በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግድቡ ባለበት ጉባ ከተማ በመከበር ላይ ሲሆን ባለፉት 4 ዓመታት ሕዝብን በማንቀሳቀስ ለግድቡ ግንባታ የተሰባሰበው መዋጮ ወይንም የቦንድ ሽያጭ 6 ቢሊየን ብር ያህልብቻ መሆኑ የመንግስትን ኪሳራ የሚሳይ መሆኑን የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን የተለያዩ ሰዎችን አነጋግሮ ባጠናከረው ዘገባ አመልክቷል።

ከ4 አመታት በፊት ለጠቅላላ ግንባታው 80 ቢሊየን ብር ገደማ ወጪ እንደሚስፈልግ የተገመተ ሲሆን፣ ወጪውን በሕዝብ ድጋፍ ሙሉ በሙሉ መሸፈን ያልተቻለው፡ መንግስት ሁሉን ያሳተፈ ብሔራዊ መግባባት ማምጣት ባለመቻሉና የግድቡን ስራ ለፖለቲካ ዓላማ እያዋለው በመምጣቱ ነው ሲሉ አስተያየት ሰጪዎች ተናግረዋል፡ በግድቡ ግንባታ ጉዳይ መንግስት ራሱን ከፍ አድርጎ ተቀናቃኞቹን በማጣጣል የሚከተለው ስትራቴጂ የልዩነት አድማሱን እንዳሰፋው የጠቆሙት አንድ ምሁር፣ በዚህ ምክንያት ብዙዎቹ ተቃዋሚዎች ግልጽ ድጋፍ በመስጠት ሕዝቡ የግድቡን ግንባታ እንዲደግፍ የበኩላቸውን እገዛ ከማድረግ መታቀባቸው:- ሕዝብ የተስተካከለ ዕይታ እንዳይኖረው አድርጎአል ብለው እንደሚያምኑ አስረድተዋል። በየኢኮኖሚ አቅማቸው የተሻሉ ናቸው ተብለው የሚገመቱ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ከግድቡ በፊት ዳቦ እና የሰብአዊ መብት ጥበቃ እንዲሁም የዴሞክራሲና የህግ የበላይነት አጀንዳዎችን ደጋግመው በማንሳታቸው በገዥው ቡድን እንደአክራሪ ኃይል መፈረጃቸው:- ተሳትፎአቸው እንዲገደብ ትልቅ አስተዋጽኦ ማድረጉንም ጠቅሰዋል።

በዚህ ምክንያት በተለያዩ በአሜሪካና በአውሮፓ ሀገራት በከፍተኛ ባለስልጣናት የታገዙ ቦንድ ማሰባሰቢያ መድረኮች የፖለቲካ ውዝግቦችን በማስተናገድ መክሸፋቸውን በማስታወስ ይህ ተደጋጋሚ ክስተት መንግስት ቆም ብሎ አካሄዱን እንዲመረምር ከማስገደድ ይልቅ ደንግጦ ብቻውን እንዲቆም ማድረጉ ሌላው ችግር ነው ሲሉ አክለዋል። ኢህአዴግ በአጼ ኃይለስላሴ ዘመን ጀምሮ የታቀደውን የአባይ ግድብ እቅድ የራሱ በማድረግ ዕውቅና ከመንፈግ ጀምሮ በሀገር ውስጥ በሕጋዊ መንገድ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለማሳተፍ እንኳዋን ፍላጎት ማጣቱንም አመልክተዋል፣ የተቃውሞ ኃይሎች አፍራሽ ሚና ብቻ እንዳላቸው አድርጎ መሳሉ ሁሉም ወገኖች በልማት ጉዳይ ላይ እንኳዋን እንዳይስማሙ እንቅፋት መፍጠሩንም አስተያየት ሰጪው ተናግረዋል። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ግማሽ ያህሉ በወጣትነት ለስራ የደረሰ ዕድሜ ላይ እንደሚገኝ ያስታወሱት ምሁሩ መንግስት ራሱ ተዋጥቶልኛል ያለውን 6 ቢለየን ብር አምነን ከሕዝብ ቁጥር ጋር ስናሰላው የተገኘው ውጤት እጅግ ደካማ መሆኑን ያሳየናል ብለዋል።መንግስት የአባይ ግድብን ብሔራዊ አጀንዳ በማድረግ ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች ድጋፍ እንዲያደርጉ በሩን ቢከፍትና ቢያሳትፍ እንዲሁም በሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ብሔራዊ መግባባትን ቢፈጥር የተሻለ ስራ መስራት ይቻላል ሲሉ ሃሳባቸውን አጠቃለዋል።

ከውጭ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን 1 ቢሊዮን ዶላር ለመሰብሰብ እቅድ የተያዘ ቢሆንም፣ እስካሁን የተሰበሰበው በ10 ሚሊዮኖች የሚቆጠር ብቻ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ።

አንዳንድ ወገኖች መንግስት በቅርቡ ከግብጽ ጋር ያደረገውን ስምምነት ተከትሎ ግድቡን ለመጨረስ:- ምናልባትም ከአንዳንድ አበዳሪ ድርጅቶች ገንዘብ ሊበደር ይችላል በማለት አስተያየት ይሰጣሉ።

## ዘመናዊ ባሪያ ፍንገላ በኢትዮጵያ

... ( ከገጽ 3 የዞረ )

ከዘበኝነት አቅም ዘርህና ጎጥህ ተቆጥሮና ማንነትህ ተጠንቶ ነው የምትቀጠረው - በር እየከፈተ መኪናን ማስወጣትና ማስገባትም ከቁም ነገር ተጥፎ እንዲህ ያለ መድሎ ይታያል።

በዕጣው አወጣጥ ችግሮች እንደነበሩበትም ይነገራል። ወያኔ ለማስመሰል ድራማው በዕጣው ቤት ይደርሳቸዋል ተብለው ከማይጠበቁ ዜጎች ከዚህም ከዚያም ለአንዳንዶች ጣል ጣል አደረገ እንጂ የአንበሳ ድርሻውን ለራሱ ካድሬዎችና ለሚፈልጋቸው ወገኖች በዕጣ አስመስሎ እንደሸለማቸው በስፋት ይወራል። ለምሳሌ በአንድ መሥሪያ ቤት ለብዙ የሥራ ሂደት ባለቤቶችና የፖለቲካ ሠራተኞች እንደደረሰና ያን የመሰለ አጋጣሚ እንዴት በዕጣ ሊወጣ እንደቻለ መነጋገሪያ እንደሆነ ከቅርብ ሰው ተረድቻለሁ። ለነገሩ በህዳሴው ግድብ ሥራ ማስጀመሪያ የመጀመሪያዋ ዕለት እንደተወለደና ስሙም ህዳሴ ለተባለ ሕጻን የህዳሴው የስልክ ሎተሪ ዕጣ የመኪና ሽልማት እንደደረሰ በሚነገርባት ሀገር፣ አንዲት የ14 ዓመት ታዳጊ ወጣት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቷ ባሳየችው የበጎ አድራጎት ሥራ የተመሰጡት ትምህርት ቤቷና ሌላ ድርጅት በጋራ ሆነው የኢትዮጵያን ዓመታዊ አጠቃላይ በጀት ሊሆን የሚዳዳው የ20 ሚሊዮን ዶላር ሽልማት እንደተቀበለችና ያንንም ገንዘብ - ድምቡሎ ሣታስቀር (እንዴት ያለ ቱጃር ቤተሰብ ነው ያላት ጃል!) ለትምህርት ቤት ግምባታ ልታውለው ለመንግሥት እንዳበረከተች በሚነገርባት የወያኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ይህ ዕጣ ሾር የለበትም ብሎ መቀበል ከየዋህነትም የዘለለ ሞኝነት ነው።

የሚውለውንና የሚያመሸውን ዜጋ በቤቱ ይቁጠረው ብቻ የምንተወው ሣይሆን እኔም ያቅሜን ተዘዋውሬ ተመልክቻለሁና እስከሞት የማይረሳኝ ዕድሉ ከገጠመኝም ምሥክርነቴን በመጨረሻም አስቀድሜ እንደጠቆምኩት ትዝናኑበት ዘንድ አንድ ወንድም ከቦስተን ማሳሹተስ የላከልኝን ኢሜይል እንዳለ በኮፒ/ ፔስት ከሥር አስቀምጣለሁ። "ያልተነካ ግልግል ያውቃል" ይባላል። እኔ በመምህር የሚታረም የፈጠራ ድርሰት የጻፍኩ ይመስል ስለ አጻጻፍ ሥልቴ አይረቤነት ያወራል። ችግራችንን ዘረዘርኩ እንጂ ሥነ ጽሑፍ አልጻፍኩም። ችግርን ለመናገር ደግሞ አንድ ሰው በልምድም ይሁን በትምህርት የሚያውቀው (አካስተኛም ቢሆን) የንግግርና የጽሑፍ ችሎታ በቂው ነው - መራቀቅና ተቺዩ እንደሚለው coherence, cohesive device ቅብጥርስ እንዲያውቅ አይጠበቅበትም። ሰላም።

## በደቡብ ክልል የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈጸሙት ከፍተኛ

... ( ከገጽ 4 የዞረ )

አቶ ሽፈራው ማንኛውንም ትእዛዝ የተቀበሉት ከአቶ መለስ መሆኑን ለቀረበባቸው ወቀሳ መልስ ሰጥተው ነበር። አቶ መለስ በህይወት ባይኖሩም አቶ ሽፈራውሽጉጤና ሌሎች የክልሉ ባለስልጣናት በክሱ አለመካተታቸው የክሱን ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ ጥሎታል።"የዘር ማጥፋትን ክልከላና ቅጣት" በሚለው አለማቀፍ ደንጋጌ ፣ የዘር ማጥፋት ወንጀል የአንድን ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ዘር አባላትን ወይም የሃይማኖት ተከታዮች ሆን ብሎ በከፊል ወይም በሙሉ ማጥፋትን ወይም የማጥፋት ሙከራ ማድረግ፣ የአንድን ቡድን አባላትመግደል፣ አካላዊ ጉዳት ማድረስ፣ በህይወታቸው ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ጥፋት በከፊል ወይም በሙሉ መፈጸም የሚሉትን ወንጀሎች መቀመጣቸውን በመጥቀስ፣ በጉራፈርዳ የተፈጸመው ወንጀልም የዘር ማጥፋት ወንጀል መሆኑን ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ የህግ ባለሙያ ገልጸዋል። ከጉራፈርዳ የተፈናቀሉ ሰዎች የት አካባቢ እንደሰፈሩና በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ በግልጽ አይታወቅም። የተወሰኑት ወደ መተማ አካባቢ ሄደው እንዲሰፍሩ ቢደረግም በውሃና በመሰረተልማት አቅርቦት ማነስ የተነሳ አብዛኞቹ አካባቢውን ለቀው ሂደዋል።